Arlington2050
Guiding Our Path
Arlington County's Comprehensive Plan Update

**COMPREHENSIVE PLAN UPDATE PROJECT**
**Guiding Principle Mini-Series**

# ሁሉን አቀፍ የእቅድ ማሻሻያ ፕሮጀክት፡ የመመሪያ መርህ ትኩረት

ዛሬ፣ ወደ የመጨረሻዎቹ ሁለት የአሜሪካ የእቅድ ማህበር መመሪያ መርሆች እየገባን ነው፡ **ጠንካራ ኢኮኖሚና ኃላፊነት የተሞላበት ክልላዊነት**

የበለጸገ አርሊንግተን በጠንካራ የአካባቢ ኢኮኖሚና ከጎረቤቶቻችን ጋር ብልህነት የተሞላ ትብብር ላይ መሰረቱን ያደርጋል፡፡ ጥንካሬን በመገንባት እንዴት እንደ ክልል እንሰራለን?

የአሜሪካ የእቅድ ማህበር
የመመሪያ መርሆች:

**ጠንካራ ኢኮኖሚ**

*ማሕበረሰቡ በኢኮኖሚው ላይ የሚታዩ አወንታዊና አሉታዊ ለውጦችን ለመቋቋምና ዘላቂነት ያለው የከተማ ልማትና የመልሶ ማልማት ስልቶችን በመቀየስ በአካባቢ ላይ አዎንታዊ ተጽእኖ ያላቸው ስራዎች እድገትን የሚያጎለብቱና በአገር ውስጥ ንብረቶች ላይ ጥገኛ እንዲሆኑ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን ማረጋገጥ።*

የማህበረሰቡ ኢኮኖሚ የአከባቢውን ህዝብ ኑሮ የሚደግፉ ስራዎችን፣ ንግድና ምርታማ ተቋማትን የሚያጠቃልል ነው። የኢኮኖሚ ጤናማነት ወሳኝ ሲሆን ለዚህም ምክንያቱ ስራን ከመፍጠርና ገቢን ከማምጣት አኳያ ጉልህ ምናን ስለሚጫወት ነው። ኢኮኖሚው ሲያድግ ወይም እየቀነሰ ሲሄድ የሰዎች መተዳደሪያም እነዚህን ተከትሎ ይሄዳል። የአካባቢ ኢኮኖሚዎች እንደ ክልላዊ፣ አገራዊ ወይም ዓለም አቀፋዊ አዝማሚያዎች ባሉ ውጫዊ ሁኔታዎች ላይ የተመረኮዘ ነው። የስራ ገበያው በአገር ውስጥ የስራ እንቅስቃሴዎች ላይ ብቻ ሳይሆን በሩቁ በሚገኙ ኩባንያዎች ወይም መንግስታት በሚደረጉ ውሳኔዎች ተጽእኖ ያርፍበታል። የሀገር ውስጥ ሀብቶችን የበለጠ መጠቀም የህብረተሰቡን ኢኮኖሚያዊ ጥንካሬ ለማጠናከርና አካባቢውን ለማነቃቃት እገዛን ያደርጋል። አንዳንድ ንግዶች በአካባቢ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ በመሆኑ እንደ የፀሐይ ኃይል ኩባንያዎች ያሉ ለአካባቢ አዎንታዊ ሚና ያላቸው ስራዎች የተሻለ ምርጫዎች ሊሆኑ ይችላሉ። በተጨማሪም ህብረተሰቡ ከውጭ በሚገቡ ሀብቶች ላይ እንደ ቅሪተ አካል ካለው ግብአት ጥገኛነት መቀነስ የሚችል ይሆናል።

ኢኮኖሚያዊ ጥንካሬ ማለት ከተግዳሮቶችና እድሎች ጋር ተስማሚነት ያለው ኢኮኖሚ መገንባት ሲሆን - ከገበያ ፈረቃ፣ የአየር ንብረት ለውጥ ወይም የህዝብ ጤና ድንገተኛ አደጋዎች አኳያ የሚታይ ነው፡፡ የተለያየ የአካባቢ ኢኮኖሚና ለሁሉም እድሎች ያላቸው ጠንካራ ማህበረሰቦች አስጨናቂ የሆኑ ክስተቶችን በተሻለ ሁኔታ ለማስተናገድ እንዲሁም በነዋሪዎችና የንግድ እንቅስቃሴዎች ላይ የረጅም ጊዜ ጉዳትን መቀነስ የሚችሉ ናቸው፡፡

የአርሊንግተን ኢኮኖሚ ጠንካራና ብዝሃነት ያለው ሲሆን በስልታዊ እቅድ፣ በጠንካራ የሕዝብ ትራንስፖርት የተደገፈ፣ ከፍተኛ የተማረ ማህበረሰብ፣ የሰለጠነ የሰው ሃይልና የዳበረ የንግድ መተላለፊያዎች ለአነስተኛ የንግድ ስራዎች ድጋፍ ቢሆንም ነገር ግን ከከፍተኛ የኑሮ ውድነት፣ ከኢኮኖሚ ኢፍትሃዊነት፣ ከቢሮ ክፍት የስራ ቦታዎችና በመንግስት የተሰጠ ውስን ስልጣን (ማለትም የዲሎን ህግ) ጫና ገጥሞታል፡፡ የወደፊት ስኬት በተለያዩ ኢንዱስትሪዎች፣ ቱሪዝምን በማስፋት፣ የቢሮ ቦታዎችን እንደገና ጥቅም ላይ በማዋልና እድገትን ከመኖሪያ ቤት አቅም ጋር እንዲመጣጠን በማድረግና ቀጣይነት ያለው፣ ዘላቂና ፍትሃዊ የኢኮኖሚ ውጤት ለሁሉም ሰው ላይ የሚመሰረት ነው፡፡

በአርሊንግተን ጠንካራ ኢኮኖሚ በሚከተሉት መንገዶች ሊሳካ ይችላል፡

- አነስተኛ የንስግድ ስራዎችና ስራ ፈጣሪዎችን በተለይም በቂ ባልሆኑባቸው አካባቢዎች መደገፍ
- የሰው ኃይል ልማትና የስራ እድል
- መፈናቀልን ለመከላከል ተመጣጣኝ፣ የተረጋጋ መኖሪያ ቤት
- የማህበራዊ ደህንነት መረቦችን ማጠናከር
- ንግዶች ክፍት ሆነው እንዲቆዩና ከችግር ወይም ከአደጋ በኋላ እንዲያገግሙ ማገዝ




*ሁሉም የአካባቢ ምክረ ሃሳቦች መለያ፣ መገናኘታቸውን እንዲሁም የአጎራባች ክልሎችን እቅዶችና አካባቢውን እንደሚደግፉ ያረጋግጡ።*

የክልል እቅድ ኤጀንሲዎች ቁጥጥር የማድረግ ስልጣኑ የሌላቸው ቢሆንም ነገር ግን እንደ የትራንስፖርት የውሃ አቅርቦት ባሉ የክልል ስርዓቶች ላይ ጠቃሚ ግንዛቤዎችን ይሰጣሉ። የትራንስፖርት እቅድ በዋነኛነት በፌዴራል የትራንስፖርት ህጎች ስራ ባለው መሰረት የተሰየሙ የሜትሮፖሊታን እቅድ ድርጅቶች (MPOs) ኃላፊነት ነው። ብዙ MPOs እና ሌሎች የክልል እቅድ ኤጀንሲዎች እንደ ክፍት ቦታ፣ የአካባቢ ጥበቃ፣ የመኖሪያ ቤት፣ የኢኮኖሚ ልማት፣ የመሰረተ ልማት መገልገያና የአደጋ ዝግጁነት የመሳሰሉ ተያያዥ ችግሮችን በመፍታት ላይ ይገኛሉ። እነዚህ በክልል የሚገኙ ኤጀንሲዎች ከአካባቢያዊ ፖለቲካ በላይ የሆኑ የጋራ ውሳኔዎችን በማስቻል በተለያዩ የአካባቢ መንግስታት መካከል ትብብር እንዲፈጠር ያደርጋሉ። የአካባቢ መንግስታት እቅዶችና ፖሊሲዎች እርስ በእርሳቸው ተጽእኖ ያሳድራሉ፣ በአዳዲስ የእድገት ቦታዎች ላይ ተጽእኖ ይፈጥራሉ እንዲሁም የዘወትር የመጓጓዣ ዘዴዎችና የዝናብ ውሃ አያያዝ ያከናውናሉ። ስለዚህ እነዚህን እቅዶች ሁሉን አቀፍ በሆነ እቅድ ማገናኘት ተደራራቢ ተግባራትን ለመረዳትና ለማስተዳደር የሚያግዝ ነው።

ኃላፊነት የሚሰማው ክልላዊነት ስኬታችን መሰረት ያደረገው በአጎራባች ክልሎች ጋር በመተባበር መሆኑን እውቅናን ይሰጣል፡፡ ግለሰቦች፣ ስራዎች እንዲሁም ስነምህዳሮች ሕጋዊ ድንበሮችን ይሻገራሉ፡፡ ከአጎራባች አካባቢዎች ጋር ትብብር ማድረግ የትራፊክ መጨናነቅን፣ የመኖሪያ ቤቶችንና የኢኮኖሚ ልማትን ጨምሮ የጋራ ችግሮችን ለመፍታት ያግዛል፡፡ ለክልላዊ መሰረተ ልማትም እንደ የሕዝብ ትራንስፖርት፣ የውሃ ስርዓትና የተፈጥሮ ሀብቶች እገዛን ያደርጋል፡፡

አርሊንግተን የመኖሪያ ቤቶችን፣ ትራንዚቶችን፣ የአካባቢ ግቦችን፣ የሰው ሃይል ልማትን፣ የጤና አገልግሎቶችን እንዲሁም የአደጋ ጊዜ ምላሽን ለማስፋት፣ ተመጣጣኝ የመኖሪያ ቤት ኢላማዎችን በማሳካትና ብልህነት የተላበሰ የእድገትና የዘላቂነት ያላቸው ተነሳሽነቶችን በማሳደግ የክልል መሪ መሆን የቻለ ነው፡፡ ሆኖም ግን የአርሊንግተን በውጫዊ ኤጀንሲዎች ላይ ያለው ጥገኝነት፣ የተገደበ የዳታ መጋራት፣ በተለያዩ አስተዳደሮች መካከል ያለ ውድድር፣ የተበታተነ የማህበራዊ አገልግሎት ማስተባበርና የስነ ሕዝብ አወቃቀር ለውጦች የሰው ኃይልን ማቆየት አደጋ ላይ ይጥላሉ፡፡ የወደፊት ስኬት ትብብሮችን በማስፋት፣ በክልላዊ የመኖሪያ ቤት መፍትሄዎች፣ በተቀናጀ የመሰረተ ልማት የመዋእለ ነዋይ ፍሰት፣ የዳታ ስርአቶች ማጋራትና እንደ AI፣ አረንጓዴ መሰረተ ልማትና ኪነህንጻን ከተፈጥሮ ጋር የሚያቀናጅ ንድፍ ባሉ አካባቢዎች ፈጠራን በማስፋፋት ላይ መሰረት ያደርጋል፡፡ ከሜትሮፖሊታንት ዋሽንግተን ምክር ቤት (MWCOG)፣ ከአጎራባች ክልሎች፣ ከፌደራል ኤጀንሲዎችና ከግል ተቋማት ጋር ያለው ጠንካራ ትብብር የክልሉን ኢኮኖሚ፣ መሰረተ ልማትና የህይወት ጥራትን የሚያዳብር ነው፡፡

በአርሊንግተን ኃላፊነት የሚሰማው ክልላዊነት በሚከተሉት መንገዶች ከግብ ሊደርስ ይችላል፡

- በMWCOG እና በሰሜን ቨርጂኒያ የትራንስፖርት ባለስልጣን (NVTA) ውስጥ መሳተፍ
- የመሬት አጠቃቀምንና መጓጓዣን ከክልላዊ የሕዝብ ትራንስፖርት ኢንቨስትመንቶች ጋር ተመጣጣኝ ማድረግ
- የክልል ቤቶችን ኢላማዎች ግብ ለመምታት ተመጣጣኝ የቤት ፖሊሲዎችን ስራ ላይ ማዋል
- የአደጋ ጊዜ ዝግጁነት፣ የውሃ አያያዝና የአካባቢ ጥበቃን ማስተባበር

**የእርስዎን አስተያየት እንፈልጋለን**

የእርስዎ ድምጽ የመግቢያውን ምእራፍ ለመቅረጽ ይጠቅማል! የእርስዎን አስተሳሰቦች፣ ሃሳቦችና ስጋቶች መስማት እንፈልጋለን፡፡

[ግምረመልሶችዎን እዚህ ጋር ያጋሩ፡፡]

በአካልና በኢንተርኔት ላይ በሚካሄዱ ስብሰባዎች እንዲሁም ዝግጅቶች በዚህ የበልግ ወቅት ይካሄዳሉ፡፡ ክትትል በማድረግ ተሳትፎዎን ይቀጥሉ፡፡